፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፮ ቀን ፪ሺ፲ በቪየና የተፈረመው ቁጥር 1340P የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር /ሃያ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. <u>**Ratification of the Agreement**</u>

The Loan Agreement No. 1340P signed on the 6th day of July 2010 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development is hereby ratified.

3. <u>**Power of the Ministry of Finance and Economic Development**</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 20,000,000 USD (twenty million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of February, 2011**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት